## ከኦስትርያ የቅንጅት ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ

# መግለጫ

በቃሊቲ እስር ቤት በግፍ ለሁለት ዓመታት ያህል ሲሰቃዩ ከቆዩ በኋላ ሃምሌ 13 1999 ዓ ም ነፃ ለተለቀቁ የቅንጂት መሪወች፣ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪወችና ጋዜጠኞችን አስመልክቶ የተሰጠ አጭር መግለጫ|፣

ከሁሉ አስቀድመን ታስረው ለተፈቱት የኢትዮጵያ ብርቅየ ልጆች እንኳን ከቤተሰቦቻችሁ፣ ከምትወዱትና ከሚወዳችሁ የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ለመገናኘት አበቃችሁ እንላለን:: ወያኔ ኢህአዴግ በአገር ቤትም ሆነ በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ብሎም የአለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማደናገር በተለመደው ተራ ፕሮፖጋንዳ አቅሙ እስከፈቀደ ድረስ በተሯሯጥበትና የቆማችሁለትን የኢትዮጵያ ህዝብ አጀንዳ በማራከስ፣ ሞራላችሁን በመፈታተን ከመቸውም ጊዜ በከፋ ሁኔታ የግፍ ቴዓትሩን በሰራበት በተለይም በዚህ ሰሞን ያጋጠማችሁ ፈተና ቀላል እንዳልሆነ ይሰማናል::

ሆኖም የሞራል ብቃታችሁ፣ ክብረት የጠነከረው ፅኑ ዓላማችሁ፣ ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያን ለማዳን ፣ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት በኢትዮጵያ እንዲሰፍን፣ የህግ የበላይነት እንዲከበር፣ ኢትዮጵያውያን ከፍርሀትና ሰቆቃ ተላቀው በነፃነት እንዲኖሩና በአጠቃላይ ሰብአዊ ፍጡር ሊኖረው የሚገባውን በቂ ኢኮኖሚያዊና ነፃ ፖለቲካዊ ህይወቱ ዕውን የሚሆንበትን ስርዓት ለመገንባት ከኢትዮጵያ ህዝብ የተረከባችሁት አደራ አሸንፎ እነሆ በእሳት እንደተፈተነ ወርቅ እናንተም እሳቱን አልፋችሁ ለዚች ታሪካዊ ቀን በቅታችኋል፣ ይህች ቀን አንዱን የድል ምእራፍ ያበሰረች ታላቅ ታሪካዊ ቀን በመሆኗ ምን ጊዜም ስናስታውሳት እንኖራለን፣ ይሁን እንጂ ትግሉ ገና ብዙ ውጣና ውረድ እንዳለው በማመን ለታለመው የመጨረሻ ግብ ከመሪወቻችን በሚፈልቁ በሳል አመራሮች በመታገዝ ብዙ የድል ምእራፎችን እንደምናስመዘግብ ምንም ጥርጥር አይኖረንም፣.

በመጨረሻም የመሪወቻችን መፈታት ዕውን ይሆን ዘንድ ለታገሉ በውጭም ሆነ በአገር ቤት ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም የውጭ ዜጎችና ሲቪክ ማህበራት በተለይም በወያኔ ኢህአዴግ የአፈና ፖሊሲ ትግሉን በአገር ቤት ማካሄድ ባለመቻሉ በውጭ አገር ሆነው እንዲያንቀሳቅሱ አደራውን ተረክበው አደራቸውን ለተወጡ የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር አባላትና በስራቸው ተደራጅተው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላደረጉ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች አድናቆታችንና ልባዊ ምስጋናችንን እያቀረብን ዛሬ ለተጎናፀፍነው ድል እንኳን አብሮ አደረሰን እንላለን፣

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

ቅንጅት የኢትዮጵያ ህዝብ ተስፋ ነው